የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 42
ADDIS ABABA 16th May 2011


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፪፻፲፰/፪ሺ፫
የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......... ገጽ ፭ሺ፰፻፳፮


CONTENTS


Regulation No. 218/2011
Wolita Sodo University Establishment
Council of Ministers Regulation..........Page 5826


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፰/፪ሺ፫

## የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፰/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. መቋቋም

፩) ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪) የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ፡፡

፫) ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል ፡፡

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 218/2011*

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF WOLITA SODO UNIVERSITY*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Wolita Sodo University Establishment Council of Ministers Regulation No. 218/2011."

2. **Establishment**

1) Wolita Sodo University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2) The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3) The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.


ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ወላይታ ሶዶ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል ፡፡

፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus in Wolita Sodo and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 16th day of May 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት